# ኀጠኝነት የጨለማ ጉዞ ነው

ታሪኩ አባዳማ ሚያዝያ 2001

መሠረቱ ህብረ-ብሔር የሆነ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ህዝብ ከዝቅተኛ የዕድገት እርከን ወደላቀ ደረጃ ለመሸጋገር ፅኑ መሠረት ላይ የቆመ ሉዐላዊነት ፣ ቀልጣፋ ማህበራዊ አደረጃጀት ፣ አሳታፊ የፖለቲካ ሥርዓት እና ጭብጥ ውጤት ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስፈልገዋል። ሁሉም አይነት የፖለቲካ ወይንም የኢኮኖሚ ፖሊሲ የራሱ ድክመት እና ጠንካራ ጎን እንዳለው ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ ህብረተሰብ ለዕድገት ያለው ፍላጎት እና ሰብአዊ ክብሩ በሕግ ተረጋግጦ የመኖር ትርጉም ፋይዳ የሚኖረው፣ ሰው ተስፋ የሚያልምበት ብቻ ሳይሆን ተስፋውን በውን ለማየት የሚችልበት ሁኔታ ከመመቻቸቱ ላይ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ዕድገት ፣ ስለ ፍትህ ፣ ስለ ሰላም እና ስለ አንድነት ብዙ አልሟል ፣ ብዙ ተመኝቷል። የተመኘውን ለመጨበጥ እጅግ ደክሟል ፣ ብዙ መስዋዕትነትም ከፍሏል። ትግሉም ሆነ መስዋዕትነቱ ዛሬም ቀጥሏል። የ1966 ህዝባዊ አብዮት የኢትዮጵያ ህዝብ ለዕድገት እና ለአንድነት መሰለፉን በጥልቀት ያመለከተ አጋጣሚ ነበር። ስለ አደዋ ወይንም ዶጋሊ ታሪካዊ ድል ሲወሳ ፣ ስለ አምስቱ አመት የጣልያን ግፍ ወይንም የሲያድ ባሬ ወረራ ሲተረክ - ያገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ ሲባል ከጎጠኞች ጋር የተካሄደውን ግብግብ ስናነሳ እና ዜጎች በጋራ ስለዚች ታሪካዊት አገር ሕልውና ሲሉ ከባንዲራው ጥላ ሥር ተሰልፈው የከፈሉትን የደም መስዋዕትነት ስንዘክር - ይህ ሁሉ ከትግሉ ጀርባ ፀንቶ የቆየውን የመላውን ህዝብ ራዕይ በግልፅ ያሳየናል።

የጣልያንን ወረራ ለመመከት ክተት ተጠርተው ከነጭፍሮቻቸው ማይጨው የዘመቱት አያቴ ቀኛዝማች ጉተማ ፊጤ አቀበት ቁልቁለቱን የወረዱት ፣ ብዙ የቤተሰብ አባላት እና የቅርብ ወገኖቼ ከተቀረው ዘማች አርበኛ ኢትዮጵያዊ ጎን ተሰልፈው ደማቸውን እንደ ጅረት ያፈሰሱት ለማንም ሳይሆን ለነበረው እና ለሚመጣው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ፤ ክብሩ የተረጋገጠ ፣ ህልውናው የተከበረ አገር ለማቆየት ነበር። አፄው 'አፈግፍገው' ወደ ጀኔቭ ሲገሰግሱ አያቴም በነፍስ የቀረ ተከታያቸውን ይዘው ወደ ቀያቸው ለመመለስ ተገደዋል። የእናቴ ታላቅ ወንድም በቀለ ገሩ ግን ማይጨው ላይ በጠላት እጅ ወደቀ ተብሎ ለቅሶ እና ተዝካሩ ከወጣ በኂላ በአራተኛው ወር ላይ እየተንፏቀቀ ወደ ቄየው ተመልሷል። ከማይጨው ተነስቶ ጅባት የንፋቅቅ መድረስ ታምር ነው።

ጣልያንን በሩቁ ማይጨው ላይ አሳፍሮ ለመመለስ የዘመተው አጎቴ ትውልድ ቀየው ተንፏቆ ሲገባ የጣልያን ታንክ ቀድሞት መንደሩን ተቆጣጥሯል። የነበረው እንዳልነበር ሆኖ ቆይቶታል። ገንጣዮችን በኤርትራ ተራሮች ላይ ሲያራውጥ የቆየው የኢትዮጵያ ሠራዊት ኂላ ላይ ያለ መሪ ሲበተን እና በህይወት የተረፈው መሀል አገር ሲመለስ የነበረው እንዳልነበር ሆኖ እንደቆየው አይነት መሆኑ ነው። የናፓልም ቦምብ ወላፈን ባደረሰበት ጉዳት ፀጉሩ ልክ እንደ ካንሰር ኬሞ ገመምተኛ ዕድሜውን ሙሉ ተመላልጦ የቀረው አጎቴ ማይጨው ወድቋል ተብሎ ተስካሩ ከተበላ በኂላ መምጣቱ ከሞት እንደተነሳ ያህል ታላቅ ደስታ ፈጥሯል። መከራው ፣ አበሳው ግን ለኢትዮጵያ ነበር።

ሻቢያ እና ወያኔ በአገር አንድነት እና ህልውና ላይ የደቀኑት አደጋ እንዲወገድ በፅኑ ያገር ፍቅር ስሜት ተሰልፈው የነበሩ እና ደማቸውን ፣ ውድ ህይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ቤት ይቁጠራቸው። ሰሜን ተራሮች ላይ የወደቁ ፣ ደማቸውን ከቀይ ባህር የቀላቀሉ - ስማቸው ግን ለማይታወቅ ወንድሞቼ ፣ የእህት እና ወንድም ልጆች ፣ የሩቅ እና ቅርብ የስጋ ዘመዶቼ ተግባራቸውን ከሁሉም ጀግና ኢትዮጵያዊ ጋር በጠለቀ ብሔራዊ ስሜት አስበዋለሁ። ሻምበል አብርሃም ረታ ፣ ወታደር ፍስሀ በቀለ ፣ ካፕቴን ተሾመ ሽጉጤ … በሰሜን ኢትዮጵያ አፅማችሁን ለመልቀም በማይቻልበት ፣ የት እንደወደቃችሁ እንኳ የሚነግረን በሌለበት ሁኔታ ከሁሉም የኢትዮጵያ ምድር ከመጣ ወገናችን ጎን ቆማችሁ ለኢትዮጵያ

ክብር ስትሉ ለከፈላችሁት ዋጋ ክብር ይሁን። እንደ አጎቴ በቀለ ገሩ አንድ ቀን ትመለሱ ይሆን የሚለው ተስፋችን ቢሟጠጥም የኢትዮጵያ ነፃነት ግን መመለሱ አይቀሬ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ ወዳለሁ።

እርግጥ ነው ነፃነታችን እና አንድነታችን ተናግቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ከምንግዜውም የባሰ ተስፋው መክኖ  አፋና በተንሰራፋበት እና ስጋት በሰፈነበት ህይወት ውስጥ እያዘገመ ነው። በታሪክ አጋጥሞት በማያውቅ ደረጃ ረሀብ ፣ በሽታ እና ስደት እያንገላቱት ነው። አበሳው ቀጥሏል - አንበሳው ሳያረጅ የዝንብ መጫወቻ ሆኗል ፤ ብሔራዊ ክብሩን በደም ያቀለመ ህዝብ የጎጠኛ መዘባበቻ ሆኗል።

ከብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት አንፃር ሲታይ ፣ ከታሪክ መከበር እና ከሰብአዊ መብቶች መረጋገጥ አኳያ ሲመዘን ፣ ከንቅዘት-አድሏዊነት መወገድ እና ከኢኮኖሚ ዕድገት አኳያ ሲመረመር ፣ በሕግ ፊት የዜጎች እኩልነት ከመረጋገጡ አንፃር ሲጤን ፤ የሕዝብ ብሔራዊ እንድነት ለዕድገት ቁልፍ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ …ወዘተ ፣ ጎጠኝነት የጨለማ ጉዞ መሆኑን የወያኔ ያገዛዝ ዘመን ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል።

አንድነት ፣ ሉዐላዊነት ፣ የሕግ የበላይነት እና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንዱ ከሌላው ተነጥሎ የማይታይ የዕድገት ቅደመ ሁኔታዎች ናቸው። በማያወላውል ሉዐላዊ መሠረት ላይ ፀንቶ ያልቆመ አገር ስለ ዕድገት ማለም ቢችልም የህዝብ አመኔታ ስለሌው ለማደግ ይሳነዋል። የአንድ ሕዝብ ህልውና መሠረቱ ያገሩ ሉዐላዊነት ዋስትና ያለው ከመሆኑ ላይ ነው። ዋስትና በሌለው ህልውና ስለዘላቂ ዕድገት መተለም አይቻልም።

ትናንት ወገኔ ያልከው ሕዝብ ፣ አገሬ ያልከው ምድር ነገ ጎረቤት ሆኖ እንደ ዳቦ እየተቆራረሰ በሚፈረካከስበት እና መገንጠል በአንቀፅ 39 ፖሊሲ በሆነበት አገር ላይ ቆሞ ዕድገት እንዴት ይቀየሳል? የትኛው ምድር ላይ ቆሞ ነው ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለነገው ትውልድ የሚተርፍ ተግባር የሚከናወነው? ለየትኛው መጭ ትውልድስ ሲባል ነው የዛሬው ትውልድ የሚደክመው? ነገ ተገንጥሎ የሌላ አገር ትውልድ ለመሆን እያሰፈሰፈ ላለው? እውን ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራዕይ ነው?

ጥያቄዬ አገሪቱን በእውር ድንብር እየገዛ ላለው ወያኔ አይደለም። በጠበቀ መሠረት ላይ ያልቆመ አገር ይዞ አገሬ ሂጄ መጣሁ ፣ አገሬ ቤት ገነባሁ ፣ አገሬ ንግድ ከፈትኩ ለሚሉ የዋህ ወገኖቼ እንጂ። መሬቱም ፣ ቤቱም ሆነ ንግዱ ነገ ወደ ጎረቤት አገር ንብረትነት የሚለወጥበት ሁኔታ በአዋጅ ተደንግጓል። ለመገነጣጠል ብናውጅም ኢኮኖሚውን እየገነባን ነው የሚል ወያኔያዊ ፌዝ የሚሰማ ሕሊና የተሸከምን ጥቂት አንባልም። የትኛውም ያገሪቱ አካል ሊገነጠል ይችላል እያልክ ያንኑ አገር እገነባለሁ ማለቱ እርስ በርሱ ክፉኛ የሚጣረስ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን የሚሽር እውነታ ነው። ልታፈርስ የፈለከውን ቤት እንኳንስ መገንባት መስኮቱን አታድስም። ይልቁንም ጥሩ ጥሩ አፍራሽ እየፈለክ ምክር ትጠይቃለህ ፣ እንዲያፍርስህ ታሰልፋለህ። ኦህዴድ ፣ ብአዴን …ቅብጥርሴ እያልክ። እግረ መንገድህንም የሚጠቅምህን ጥሩ ጥሩ ዕቃ ከሚፈርሰው ቤት ታሸሻለህ ፣ ትዘርፋለህ። ኢትዮጵያ እየተዘረፈች ነው።

ጎጠኝነትን ምርኩዝ አድርጎ የተነሳ የፖለቲካ ሀይል በአገሪቱ ውስጥ የሚነሱ ፖለቲካዊ ሆነ ማህበራዊ ጥያቄዎችን የሚመዝነው በጎጥ መሥፈርት ነው። ካርታ ቢስል ፣ ታሪክ ቢያወራ ፣ የፖለቲካ ሹመት ቢሰጥ ፣ ምርጫ ብሎ ቢሰለፍ ፤ ከትንሿ የንግድ ፈቃድ እስከ ግዙፍ የኢኮኖሚ አውታር ቁጥጥር በሚመለከት …ወዘተ ሁሉም ነገር በጎጥ መነፅር ተመዝኖ የጎጥ ክፍፍል የሚጠናከርበትን መሠረት ለማፅናት የሚከናወን ነው። ነገ ሲገነጠል እራሴን ችያለሁ የሚያሰኝ ሀብት ለማካበት የሚደረግ ሩጫ።

ህወሓት በሥልጣን ላይ ከወጣበት ዘመን አንስቶ እየተገበሩ ያሉትን ጉዳዮች ማየቱ ብቻ ለዚህ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል። ብሔራዊ ጥቅም ተጨፍልቆ ሁሉም ነገር በጎጥ ረድፍ ገብቷል።

ኑሮውን ለማሸነፍ እና ለመሻሻል ደፋ ቀና የሚል ታታሪ ሕዝብ የድካሙ ውጤት ተጠቃሚ የሚሆነው በራሱ ሙሉ ፈቃድ ሥልጣን ላይ በተቀመጠ መንግሥት ብቻ ነው። ይህ መንግሥት ተጠሪነቱም ሆነ

ተጠያቂነቱ ለመላው ዜጋ ይሆናል። በሥልጣን እንዲቆይ ወሳኙ ጉዳይ ብቃቱ እንጂ የዘር ግንዱ አይደለም። በዘር ግንድ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሥልጣን ብሔራዊ ራዕይ ሊኖረው አይችልም ፤ የመላውን ዜጋ አመኔታ ሊያተርፍ የሚችልበትን መንገድ አይገነባም። ዕውቀት እና ጥበብ ለዕድገት አስፈላጊ ነው ፣ ታዲያ በትምህርት እና በጥረት እንጂ ጥበብን በዘር አያገኙትም።

ፍትህዊ የፖለቲካ ሥርዓት በማያቋርጥ ፍጅታ እና ምርታማነት ሂደት የተወጠረ በመሆኑ ሁልግዜም በተህድሶ እና በፈጠራ ሥራ እራሱን ያሳድጋል። ትርፋማነትን ግብ ያደረጉ አዳዲስ ሀሳቦች እና ያሠራር ልምዶችን በማዳበር ይንቀሳቀሳል። ለዕድገት መሠረቱ ሰው መሆኑን በአፅንኦት ይቀበላል። ሰው ለትርፋማ የምርት ተግባር እንዲሰማራ ፣ ለሥራ ያለው አመላካከት እንዲጎለብት ያበረታታል። ሠርቶ ለመኖር እና ለማደግ  የሚያበረታቱ መሠረታዊ ቀዳሚ ነገሮች መመቻቸት እንዳለባቸው ያምናል - ለዕድገት ቅድመ ሁኔታው ሰላም እና መረጋጋት በመሆኑ ሕግ እና ሥርዓት መስፈኑን ያረጋግጣል።

የዜጎች በነፃነት መንቀሳቀስ ፣ መማር እና ሙያን ማሻሻል ፣ በራስ መተማመን መንፈስ እንዲጎለብት ተግቶ ይሠራል። ከሁሉም በላይ አገር እና ብሔራዊ ማንነት ነጥሮ እንዲወጣ እና ብሔራዊ ጥቅም አስተማማኝ የደህንነት ዋስትና እንዲያገኝ ተገቢውን መዋቅር ይዘረጋል። ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል ነው በሚለው መርህ እና ዕምነት ላይ የተገነባ ግልፅ ሕግጋትን በመቅረፅ ዋልጌ ሹማምንት  ሳይቀሩ ፣ ከበርቴዎች እና የፖለቲካ ሰዎች ጭምር በህግ የሚዳኙበት እና እንደ ጥፋታቸው መጠን ሳይውል ሳያድር ቅጣት የሚቀበሉበት ሥርዓት ይገነባል። የመናገር እና የመፃፍ መብቶች የህግ ዋስትና ተስጥቷቸው በዳበረ የአፃፃፍ እና ሀሳብ ላይ የተመረኮዙ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ይከናወናሉ። ሁሉም ዜጋ በህግ ጥላ ሥር የመኖር ዋስትና ሲኖረው ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገውም የግንባታ መሠረት ለመጣል ይነሳሳል። አገር የሚያድገው በሕግ የሚመካ ሕዝብ ሲኖረው ብቻ ነው።

ደግ ይባል በነበረበው ዘመን - ቢያንስ አገር ገንጥሉ የሚባል አዋጅ ሕግ ሆኖ ባልታፃፈበት ዘመን የሰማሁትን ምሳሌ በማቅረብ ሀተታዬን ልደምድም። ያኔ ድሮ ፣ ወያኔ እጅ ሳንወድቅ አዛውንቱ በመንደራቸው የሎሚ ችግኝ ለመትከል ቁፋሮ ይዘዋል። መንገደኛው ጠጋ ብሎ 'አባቴ ፣ ይህ ሎሚ አብቦ ለማፍራት ብዙ ዘመን ይጠይቃል ፤ ፍሬውን ለማየት እርሶ በሕይወት የሚኖሩ አይመስለኝም እና ለምን ይደክማሉ?' ብሎ ይጠይቃቸዋል። 'አይ ወዳጄ እኔ ባልደርስበት ልጆቼ ፣ የልጅ ለጆቼ ይጠቀሙበታል' ብለው መልስ ሰጡ ይባላል። አዛውንቱ ለመጭው ትውልድ የሚተርፍ ስንቅ ለማዘጋጀት በሙሉ ዕምነት እየሠሩ ነበር። የተከሉት ችግኝ ለመጭው ትውልድ እንደሚደርስ እርግጠኛ ነበሩ። ያኔ የመገንጠል ፖሊሲ ስጋት አልነበረም ፣ አገር እንደ ዳቦ ሊፈረካከስ ይችላል ብለው አይሰጉም። ጎጠኝነት የሚያኮላሸው ትልቁ አሴት ልበ-ሙሉነት ነው። ልበ-ሙሉ ያልሆነ ህዝብ እርስ በርሱ አይተማመንም ፣ ዛሬ ዘርፎ ፣ ዛሬ በልቶ ማደርን ይመርጣል። አዛውንቱ ያኔ የተከሉት የሎሚ ችግኝ የተከሉበት መሬት ዛሬ ሱዳን ትውሰደው ወይም ወደ ኤርትራ ግዛት ይጠቃለል በውል አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ጎጠኝነት የጨለማ ጉዞ መሆኑን ብቻ ነው።